# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 20

ግንቦት 28 ቀን 2014ዓም( 05-06-2022)

በተከታታይ ስናቀርብ የነበረው ዘገባ በብዙ መልኩ አገራችን ያለችበትን አደገኛ ሁኔታና ሕዝባችን የሚገፋውን አስከፊ ኑሮ የሚገልጽ ነበር፤የአሁኑም ዘገባችን ከዚያ አይርቅም ወይም የተለዬ አይደለም። ይህንን ስንል መጥፎና አስከፊ ሁኔታዎችን ብቻ እዬፈለግን በማቅበር የሕዝብን ስሜት ለመጉዳትና ሃዘን ውስጥ ለመክተት ወይም በሥልጣን ላይ ያለውን አካል ለማጥቆር ሳይሆን በመሬት ላይ ያለውን ገሃድ እውነታ ተንተርሰን ነው። መንግሥታዊና ቡድናዊ በሆኑ ሃይሎች በግፍ የሚገደል፣የሚፈናቀል የሚታፈንና የሚሳደድ ፣በኑሮ ውድነት የሚጠበስ፣፣በሰላም እጦት የሚሰቃ፣በሽብር እርምጃ የሚጨፈጨፍ ሕዝብ ባለበት አገር ውስጥ ሊነገር የሚችለው ይህንኑ የመከራ ታሪክ እንጂ የደስታና የፌስታ ትርክት አይሆንም።ሃዘኑን በደስታ፣እርሃቡን በጥጋብ፣መከራውን በድሎት፣ሽብሩን በሰላም፣ ማጣቱን በማግኘት፣ዘረፋና ቅሚያውን በሽልማት ተርጉመው የሚናገሩ ቢኖሩ የተጠያቂው አካል አባላትና የጥቅም ኢጋሮች ናቸው።

ተርቦ የምግብ እርዳታ ያለህ የሚል ሕዝብ፣አንድ ሊትር ወተት 80 ብር በገባበት ፣በርሃብ የናት ጡት ደርቆ ሕጻን ልጅ የሚጠባው ሲያጣ የሚያሰማውን የጣር ድምጽ የሚሰማ፣ዜጋ በጎሳ ማንነቱ ሲፈናቀል፣ ከሥራው ሲባረር፣ያዬ ሰው ህሊናውን ካልሸጠ በስተቀር የክህደት ምስክርነት አይሰጥም።ለተጠያቂው አካልም ጥብቅና አይቆምም።እኛም ምንም መሪር ቢሆን ያለውን ሳንደብቅና ሳንቀንስ በቻልነው መጠን የምስክር ቃላችንን በጽሁፍና በeምጽ ማሰማታችንን እንቀጥልበታለን።ለድምጽ አልባዎቹ ግፉኣን ድምጽ እንሆናለን።

የግንቦትን ጠራራማ ወር አልፈን የሰኔ ወርን ስንጀምር የምናስበው ከወር በኋላ በአገራችን ሰማይ ላይ ጭጋጋማና ጥቁር ደመና ፣ብሩህ የበልግ ወር ሳይሆን የዶፍ ዝናብ ፣ የጎርፍ፣የብርድና የቆፈን ክምችት የተሸከመ፣ ከመልካሙ መከራው የበዛ የክረምት ጊዜ እንደሚመጣ ነው።ክረምት ከገባ በገጠር የሚኖረው በከተማ ከሚኖረው ጋር ለመገናኘት የማይችልበት የመንገድ ብልሽትና የወንዝ ሙላት የሚከሰትበት ጊዜ ነው።ክረምት ከመግባቱ በፊት የሚታረሰው ታርሶ የደረሰው ታጭዶ ጎተራ የሚገባበት፣ የሚያፈስ ጣራ የሚከደንበት ጊዜ ነው።ቀድሞ በቂ እህል ያልሰበሰበና የቤቱን ጣራ ያልጠገነ ሰነፍ ለእርሃብና ለዝናብ የተጋለጠ ይሆናል።ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ቢሯሯጡ ጠብ የሚል መፍትሔ አይኖርም።በስንፍና ወይም ግራ በመጋባትና በማጣት ለሚገጥመው ችግር ዝግጅት ለማድረግ ያልቻለው የጨነቀው በዚህ ሃረግ ያለበትን ሁኔታ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።

ሃምሌ ናሴ መጣ ሁለት ወር ክረምት፣

ሳልዘጋጅለት ቤት ሳልሰራለት።

አባባሉ ለክፉ ቀን ወይም ሊከሰት ለሚችል አደጋ ቀድሞ የመዘጋጀቱን ጥቅም የሚያሳይ መልእክት ያዘለ ነው።ያልተዘጋጀ ናወጀ! ያልጠረጠረ ተመነጠረ!ይሆናልና።

ይህንን የክረምት ወቅት ከአገራዊ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር አገናዝበን ስንተረጉመው የሚያሳዬን ደግሞ ጊዜውን ጠብቆ እንደሚወርድ በነጎድጓድ የታጀበ ዶፍ ዝናብ በሚመስል የተጠራቀመው የሕዝብ ብሶትና ተስፋ መቁረጥ ሳቢያ የለዬለት የሕዝብ ተቃውሞና አመጽ ሊወልድና ለስርነቀል ለውጥ የሚያበቃ ሕዝባዊ ማእበል ሊከሰት እንደሚችል የምንገምትበት ወቅት ላይ መሆናችንን ነው።ለዚያ

የሕዝብ ሞገድ ምክንያቶች አንዱ የሆነው ባለፉት ዘገባዎቻችን ካቀረብነው ሁኔታ በባሰ ደረጃ የመንግሥት ጸረ ሕዝብ እርምጃ በስፋት መቀጠሉ ነው።በተለይም በአማራው ማህበረሰብና ለሱም መከታ በሆነው ፋኖ ላይ የከፈተውን ዘመቻ ይበልጥ አጠናክሮታል። በዋናው ጦር አዛዥ በአብይ አህመድ ትእዛዝ የመከላከያ ሚኒስትሩ አብርሃም፣ የጦር አዛዡ ብርሃኑ ጁላ እንዲሁም የደህንነት ቢሮ ሃላፊው ተመስገን ጥሩነህ ምክትል ኤታማጆር ሹሙ አበባው ታደሰ ከብአዴን ከተባለው አሽከር ድርጅት ጋር በመተባበር ፣የሱዳንን ወረራ መመከት ያልቻለና ያልደፈረ ሠራዊት በተለያዩ ቦታዎች አሰማርቶ በራሱ ሕዝብ ላይ የሽብር ዘመቻውን አፋፍሞታል። ይህ ወራሪ ቡድን በጎጃም፣በሸዋ፣ በወሎና ጎንደር ከባቢውን የጦር ቀጠና አድርጎ የገደለውን ገሎ የማረከውን በፍርድ ቤት ለመቅጣት የጦር ፍርድ ቤት ማቋቋሙ ሲሰማ ምን ያህል ለአማራው ማህበረሰብ ያላቸውን ጥላቻ ያሳያል። በደቡብና በምዕራብም እንዲሁ ሕግ የማስከበር እርምጃ በሚል ሽፋን የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን በማደን ላይ ነው።በአዲስ አበባና በሌሎቹም ከተማዎች ተቃዋሚ ናቸው ያላቸውን እያፈነ ወደ እሥር ቤት በመወርወር ላይ ይገኛል። ቢሆንም እንዳሰበውና እንዳቀደው የሕዝቡን „ቃውሞ ለማገድ የሚያደርገው ሙከራ አልተሳካለትም።በተለይም በአማራው ማህበረሰብ በኩል ለፋኖ የሚሰጠውን ድጋፍና ከለላ እንዲሁም ተሳትፎ ጨመረው እንጂ አልቀነሰውም።በዚህ የተበሳጨው የመንግሥት ሃይል በሕዝቡ ላይ ጫናና ማስገደዱን በማጠናከር ጥቂቶች ከጎኑ እንዲቆሙ ለማድረግ ሲችል የፋኖ ቤተሰቦችን ሳይቀር በሚያደርሰው ማንገላታት ይበልጥ የተጠላ አድርጎታል።ባካሄደው ከበባ ብዙ ህይወት ከሁለቱም በኩል የጠፋ ሲሆን ብዙዎችም ቆስለዋል።የመንግሥት ሃይል ለሁለት ተሰንጥቀም ጎራ ለይቶ መታኮሱ ለመንግሥት ያልታሰበ መርዶ ሆኗል።

ዘመነ ካሴ የተባለውንና ሌሎቹን የፋኖ መሪዎች ከቦ ለመያዝ ወይም ለመግደል ብዙ ወታደር ቢያሰማራም አልተሳካለትም።የ85 ዓመት እድሜ ያላቸውን የዘመነ ካሴን መነኩሲት እናት ከማንገላታቱም በላይ መቀነት ፈትቶ ያለቻቸውን ትንሽ ብር ነጥቆ መውሰዱ የተሠማራውን አውሬ ጦር ምንነትና የመሪዎቹን ጭካኔ በጉልህ ያሳዬ ተግባር ነው።በዚህም አላበቃም ባለፈው ሳምንት አንድ የሦስት ዓመት ሕጻን በፋኖ አባቱ ምክንያት ታፍኖ የመወሰዱና በእስር ቤት ለስድስት ቀናት ከቤተሰብ ተለይቶ መሰቃዬቱ ጉድ ሲባል ከዚያ የባሰ ከሁለት ቀናት በፊት በግ ይጠብቅ የነበረ የ13 ዓመት ታዳጊ ልጅ ወራሪዎቹ ሰው ገለው ሲጎትቱ አይቶ በፍርሃት እቤቱ ሮጦ ሲገባ ተከታትለው ከወላጆቹ ፊት በጥይት ደብድበው ገለውታል።በወሎ ክ/ሃገር በወረባቦ ሃርቡም፣ አንድ ፋኖ በመሰወሩ የሰባት ወር እርጉዝ የሆነች ሚስቱን ለሳምንት አስረው ሲያሰቃዩ የአገር ሽማግሌዎች ገብተው በሰላም ንግግር ስምምነት ምክንያት የተሰወረው ፋኖና ሌሎቹም ከጫካ ወጥተው እጃቸውን ከሰጡ በኋላ የመንግሥት ሃይሎች ቃላቸውን አጥፈው እስር ቤት ወርውረዋቸዋል።

እነዚህ ከአውሬ የማይሻሉና ከማህበረሰቡ ጋር በቋንቋ የማይግባቡ በስነምግባር የማይጣጣሙ የሚፈጽሙት አድራጎት የሥርዓቱን ምንነት የሚገልጽ ነው።በስርዓቱ ፈቃድና ትዕዛዝ ፣እውቅናና ይውንታ የሚፈጸም ወንጀል ስለሆነ የሥርዓቱ ተጠሪዎች በሙሉ ለሚፈጸመው ሁሉ ተጠያቂዎች ናቸው።እነዚህ ገዳዮችና መሪዎቻቸው የሚፈጽሙት ወንጀል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።

ከሃያ በላይ የሚሆኑ ጋዜጠኞችን ከያሉበት አፍኖ ማሰር፣ በየእስር ቤቱ መደብደብና ማሰቃዬት የተለመደ ድርጊት ሆኗል።በድብደባም ህይወታቸው ያለፈ እንዳሉ ታውቋል።በጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ላይና፣በፋኖዎች ላይ የደረሰው ድብደባ ከመቁሰል እስከሞት አደጋ ያስከተለ ጭካኔ ነው። ተመስገን ደሳለኝ ሆስፒታል ሄዶ እንዲታከም ሃኪሞች ቢያዙም ወደ ሆስፒታል ሲሄድ ሳይታከም ከመንገድ ላይ እንዲመለስ ባለሥልጣኖች አዘው ከነህመሙ እንዲቆይ ተደርጓል።

አሳዶ ማፈኑና ማሰሩ በመንግሥት የመገናኛ ዘርፎች ተገልጾ ሕዝብ በገሃድ ያወቀው ሆኖ ሳለ መንግሥት ዓይኑን በጨው አጥቦ በቃል አቀባዩ በለገሰ ቱሉ በኩል አንድም ጋዜጠኛ አልታሰረም የሚል መግለጫ አውጥቷል።ይህ ከማን አለብኝ ወይም ሕዝቡ የማስታወስ ችግር አለበት ብሎ ከመገመትና ከመናቅ የመጣ እብሪት ከመሆን የዘለለ አይደለም።

የፖለቲካ ድርጅት አባላትንና ይቃወሙኛል ብሎ ያሰባቸውን ማሳደድና ማሰር ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውንም ጭምር ማንገላታትና ማስጨነቅ የተለመደ ሆኗል። ቤተሰቦች ከሚኖሩበት የኪራይ ቤት ማሶጣትንም የመሰለ ጭካኔ ተፈጽሟል። በጎጃም ፋኖ ባሏ በመሰወሩ ምክንያት የልጆች እናት የሆነች  ሚስት ከምትኖርበት ቤት ኪራይ  በባለሥልጣኖች ትዕዛዝና ባከራዮቹ ተባባሪነት ከቤቷ ወጥታ ሜዳ ላይ ተጥላለች፤ለጊዜው ከዘመድ ጋር የተጠጋች ቢሆንም የልጆቿ የትምህርትና የሷም ኑሮ መናጋቱን ገልጻለች፤የወደፊት እጣዋም ምን ሊሆን እንደሚችል ባታውቀውም ከዚህ የባሰ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅትም።።በጣም የሚያሳዝነው ቤት አከራዮቹ የጥቃቱ አካል መሆናቸው ነው። እንዲህ አይነቱ አድርባይነትና ፍርሃት ባለበት አገር ነው አምባገነኖች ያሻቸውን እያደረጉ በሥልጣን ላይ መቆዬት የሚችሉት።እንደነዚህ አይነቶቹ አድርባይና ፈሪዎች ቢያስቡት ኖሮ ፋኖ የሚታገለው ለራሱና ለቤተሰቡ ጥቅም ሳይሆን ለመላው የአማራ ብሎም እነዚህን የቤት አከራይ የሆኑትን ጨምሮ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና እኩልነት ብሎም ሰላማዊና የተሻለ ኑሮ ነው። በስንዴ ውስጥ እንክርዳድ መኖሩ የተለመደና የሚታወቅ ስለሆነ የነዚህ አይነቶቹ የጥቅም እስረኞች መኖራቸው አያስደንቅም። በቤት አከራዮች ዙሪያ ብቻም ሳይሆን በማንኛውም የሙያ ዘርፍና የማህበረሰብ ክፍል ለሆዳቸው ያደሩ፣አገራቸውን የሚከዱ፣ብትበታተን ደንታ የሌላቸው፣ወገኖቻቸውን አሳልፈው የሚሰጡ መኖራቸውን በገሃድ ታዝበናል።መንግሥት ካለነዚህ ደካማ  ሆዳደሮች አቅመቢስ ነው። የምሳሩ ብረት ካለጠማማ የእንጨት እጀታው ብቻውን ዛፍ አይቆርጥም፤ካለነዚህም ጠማማ ሰዎች ጨቋኝ መንግሥት አይኖርም፤አያጠቃም።የውጭም ወራሪ ሃይል የሚሳካለት በባንዶች ትብብር ነው።ይዋል ይደር እንጂ የከሃዲዎችና የመንግሥታቸው መውደቂያ እሩቅ አይሆንም።ሕዝብን ያስለቀሰ  መንግሥት ዕድሜው አጭር ነው።ይህንን ታሳቢ በማድረግ ነው ያለውን መጭ ሁኔታ በክረምቱ ወቅት የሚመጣውን ነጎድጓዳማ ዝናብና ጎርፍ መስለን የገለጽነው።አሁንም እንላለን በአገራችን የሕዝባዊ አብዬት እንደ ነጎድጓዳማ ዝናብ ለመውረድ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ተንጠልጥሏል፤ የቀናት ግፋ ቢል የወራት ጉዳይ ነው ለውጥ ይመጣል፣አይቀሬ ነው።ለውጡ ግን ትክክለኛ አቅጣጫውን ይዞ እንዲጓዝ፣ለጥገና ሳይሆን ለስርነቀል ለውጥ እንዲበቃ አስፈላጊው ዝግጅት መኖር እንዳለበትም አሳስበናል፤አሁንም አጥብቀን እናሳስባለን።

በኑሮ ውድነትና በሰላም እጦት በሚበሳጨው ሕዝብ ላይ አፈናና ከበባ ሲጨመርበ የመንግሥት ዕድሜ እያጠረ መሄዱ የሚካድ አይደለም።ለአመጽ የሚቀሰቅሱ ሁኔታዎች ተሟልተዋል የሚቀረው አመጹን ሊመራ የሚችል የተደራጀ ሕዝባዊ አካል መኖር ነው። ክረምት ከመግባቱ በፊት መዘጋጀት የግድ እንደሚል ሁሉ ሕዝባዊ አመጹም ከመነሳቱ በፊት የሚመራና መልክ የሚያሲዝ አካል መፍጠር አስፈላጊና ግዴታ ነው።ባለፉት  50 ዓመታት ከዬካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ የተካሄዱት የሕዝብ ተቃውሞዎች የሚፈለገውን ስር ነቀል ለውጥ ሳያመጡ የአምባገነኖች በሥልጣን ላይ የመቀመጥ ዕድል የፈጠረው የሕዝቡን ትግል በቆራጥነትና በዓላማ ጥራት የሚመራ ፣ራዕይ ያለው አመራር ወይም ድርጅት ባለመኖሩ ነው።አሁንም ይህ ክፍተት እስካልተደፈነ ድረስ ውጤቱ ያው በአምባገነኖች ክርን ሲደቆሱ መኖር ይሆናል።

የአሁኖቹን አምባገነኖች ካለፉት ልዩ የሚያደርጋቸው ቢኖር የቀድሞዎቹ ፍላጎታቸው ያልተቆራረሰች ኢትዮጵያን መግዛት ሲሆን ከሰላሳ አንድ ዓመት ወዲህ ያሉት ግን ተበታትና የእኛ ነው የሚሉትን ከባቢ ቦጭቀው መግዛት ነው።

ሊመጣ የሚችለውን ለውጥ ለማደናቀፍ የተያዘው ሌላው መንገድ የየከባቢውን ሽማጌሌዎችና የሃይማኖት አባቶች መንግሥትን ደግፈው እንዲወጡና ሕዝቡን ለድጋፍ እንዲቀሰቅሱ ማድረግ ነው። ይህንን አደረጉ የተባሉት ሰዎች አድራጎታቸው ከሕዝብ የሚነጥላቸው እንጂ የሚያቀራርባቸው አልሆነም።ጥርስ ተነክሶባቸዋል።እነዚህን ያዩ ያገር ሽማግሌና የእምነት አባቶች በሕዝቡ እንዲከበሩና እንዲደመጡ ታሪካቸውም በአሳፋሪ ቀለም እንዳይጻፍ የሚፈልጉ ከሆነ መንግሥትንና ደጋፊዎቹን ልጆቻችንን አታሳዱ፣ሕግና ፍትህ ይከበር፣ለሕዝቡ ጥያቄ ተገቢ መልስ ስጡ፣ያገራችንን አንድነትና ዳር ድንበር አስከብሩ፣ሰይጣናዊ የሆነውን የጎሳ ፖለቲካና አገራዊ አወቃቀር አሶግዱ ብለው መጠዬቅ ይገባቸዋል፤ይህንንም ያደረጉና በማድረግም ላይ ያሉ የእምነት አባቶችና የሃገር ሽማግሌዎች ብዙ ናቸው።ለነዚህ ዕድሜና ጤና እንመኛለን።

በአብይ አህመድ የሚመራው የአነጉ ኦሕዴድና አጫፋሪዎቹ የብልጽግና ተብዬው ስብስብ ከወያኔ ጋር ለመደራደር ሁሉንም አማራጭ እዬተጠቀመ ይገኛል።ለአማራጮቹ እንቅፋት የሆነውን የአማራውን ማህበረሰብ ማንበርከኩ የመጀመሪያው የስምምነት መቋጫ ነው።ከዚያም የወልቃይት ጠገሌንና የራያን መሬት አሳልፎ የመስጠቱ ውሳኔ ለትግራይ አገር ምሥረታና ለኦሮሙማው አገር ምሥረታ የመሠረት ድንጋይ ይሆናል።በዓላማ የማይነጣጠሉት እነዚህ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ወያኔ ከሰሜን ኦሕዴድ ኦነግ ከደቡብና ከምዕራብ የግዛት ወሰናቸውን አስፍተው ሌላውን እያቁረቆዙና እዬኮረኮሙ የመኖር ዕቅዳቸውን ለማሳካት ከመጋረጃው በእስከጀርባ ስምምነት ላይ እንደደረሱ ብዙ አመላካቾች ታይተዋል።

ወያኔ ኤርትራንም ወሮ የግዛቱ አካል ለማድረግ የቆዬ ፍላጎትና ምኞት አለው።ትግራይ ትግርኛ የሚለው በጣሊያኖች የተነደፈ አገራዊ ምሥረታ በወያኔ ልብ ውስጥ የተቀረጸ ዘመን የማይሽረው ዓላማ ነው። ለዚያም ኢሳያስ አፈወርቂንና የሚመራውን መንግሥት ለማሶገድ ተቃዋሚ ናቸው ያላቸውን የኤርትራ ተወላጆች አሰባስቦ ለመገልበጥ ጦሩን አሰማርቶ በተደጋጋሚ ሙከራ አድርጓል፤አሁንም በመሞከር ላይ ነው።የምዕራቡ በተለይም የአሜሪካ መንግሥት በኢሳያስ አልበገሬነት ላይ ባለቸው ጥላቻ፣ የቻይናንና የሩስያን በከባቢው ተቀባይነት የማግኘቱ ስጋት፣በኢትዮጵያም ላይ ለሚያደርጉት ተጽእኖ አንዱ መሣሪያቸው ወያኔ ስለሆነ የመሣሪያም ሆነ የገንዘብ ብሎም የፖለቲካና የዲፕሎማሲ እርዳታቸውን በገፍ ይሰጡታል።ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ከውጭ ታሳድራለች እንደሚባለው፣መንግሥት በመገልበጥና አገራት በማፈራረስ ልምድና ችሎታ ያላቸውን የምዕራቡን በተለይም የአሜሪካንን ቡራኬ ለማግኘት ወያኔ የማያደርገው ድርጊት የማይፈጽመው ክህደት የለም።ይህንን ተልእኮ ለማስፈጸም በአስታራቂነት የተመደበው የቀድሞው የናይጀሪያ መሪ አባሳንጆ መቀሌና አዲስ አበባ እዬተመላለሰ ሁለቱም የሚፈልጉትን እንዲያገኙ ያደረገው ጥረት ውጤት ላይ መድረሱን ፍንጭ ሰጥቷል።በአንድ ቀን ውስጥ መቀሌና ቦሌ ገብቶ ለምስራቹ ፌስታ ሳይሆን አይቀርም ከአብይ ጋር በእርሻ መስክ መሃል ለመዝናናት ባሌ ተያይዘው ሄደዋል።የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገሩና በራሱ ላይ የሚጫወቱበትን ጢብጢብ ጨዋታ አልተረዳውም።ወያኔን አሸባሪ ብሎ የፈረጀውም የሕዝብ ምክር ቤት ተብዬው የአብይ አህመድ ካሮሳ ስብስብ ስለጉዳዩ የሚያውቀው የለም።ሌላው ቢቀር አብይ አህመድ የሚመራውን መንግሥት እንዴት ከምክር ቤቱ እውቅና ውጭ አሸባሪ ብሎ ከፈረጀው ወያኔ ጋር ውይይት ብሎም ስምምነት ይደረጋል ብሎ አልጠዬቀም።ሊጠይቅ የማይችልበትም ምkneያት አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ እንዲሉ ከ!,ቱም የአንድ ሳንime ሁለት ገጾች ስለሆኑ ነው።

በሌላም በኩል ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ስብስቦች ያደረጉት ጥምረትና ከአሜሪካ መንግሥት ሹማምንት ጋር ያደረጉት መቀራረብ ለዚሁ የምዕራቡ እኩይ ሴራ መሳካት የታሰበ ዝግጅት ነው። የቀኝ አክራሪዎችም የዚያው ጎራ አባላት ናቸው።ይህንን በተግባር ለማለጽ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮና  በአገር ቤትም በአሜሪካ ኤምባሲ ግቢ ሲርመሰመሱ የታዩት የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ለዚያ እኩይ ዓላማ የሚረዳ ድጋፍ ለመሰብሰብና ቃል ኪዳን ለማሰር ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገሩ ልዑላዊነትና ነጻነት ካሰበ በምዕራባውያንም ሆነ በሌላ የውጭ ሃይል ድጋፍ ለውጥ አመጣለሁ ብሎ ማሰብ አይኖርበትም።በነሱ እርዳታና እውቅና የሚመጣ ለውጥ የሥርዓት ለውጥ ሳይሆን የመሪዎች ለውጥ ነው።ከድጡ ወደማጡ ነው።ለነሱ ያደረ ቡድን ሕዝብ ቢገል ቢያሳድድ ደንታ የላቸውም።ላለፉት 31 ዓመታት ያዩነውም ይህንኑ ነው።ለነሱ ዴሞክራሲ ማለት ያሻቸውን የሚያደርጉበት፣ጥቅማቸውን የሚያስከብሩበት ሁኔታ ሲሰፍን ብቻ  ነው። በከባቢው ሊኖራቸው የሚፈልጉትን የበላይነትና ቁጥጥር ለማጥበቅ ሲሉ የማይፈጽሙት ወንጀልና የፖለቲካ ዝሙት የለም።ለነሱ ዓላማ አማራው እንደማይመቻቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ።ቢችሉ የአማራውን ሆድ አደሮች በጥቅም ይገዛሉ፤ካልሆነላቸውም አማራውን ለማንበርከክ የወልቃይትንና የራያን መሬት ለወያኔ አሳልፎ መስጠት እንደ ዋና መፍትሔ አድርገው ይጠቀሙበታል። በስምምነት አለያም በሃይል ለመውሰድ የሚያስችል ዝግጅት የአሜሪካኖቹ አማራጭ መንገዶች ናቸው። አሁን ደግሞ ወያኔ ሌላ አማራጭ ይዞ ብቅ ማለቱ ተሰምቷል፤ ያም የወልቃይት ጠገዴና የራያ መሬት የራሱ አለመሆኑን በማመን 6 ቢሊዮን ብር ልክፈልና ልውሰድ ብሎ የመጠዬቁ ዜና ነው።አብይ አህመድ እንኳንስ ብር ተከፍሎት ይቅርና የሱን መንግሥት የማይቀናቀኑት ከሆነ ወያኔ እስከ ደሴና ባሕር ዳር መጥቶ ቢይዝ ደንታ የለውም።ከነሱ ጋር ግብግብ ያስገባው በሥልጣኑ ስለመጡበት ብቻ ነው።ለኦሮሙማው ቡድን ወልቃይትና ጠገሌ እንዲሁም ራያ የባዕድ አገር ሰው የሆነው የአማራው ይዞታዎች ስለሆኑ አያሳስበውም።

ኦሕዴድ- ኦነግ በአዲስ አበባም ላይ የሚያካሂደው የመዋጥ እንቅስቃሴ ቀጥሏል።በዬትምህርት ቤቱ የኦነግን ባንዲራ የመስቀሉና የቄቤ መዝሙር የማዘመሩ ግዳጅ የሕዝቡን ተቃውሞ የጋግሎታል። በዚህ ሳምንት በአዲስ አበባ ገላን በተባለው አካባቢ በሚገኘው ት/ቤት ውስጥ የተቀሰቀሰው የተማሪዎችና የወላጆች ተቃውሞ ከባንዲራ በላይ ነው።ኦሕዴድና ኢጋሮቹ የማይፈልጉት ብሎም የሚያሳብዳቸው መፈክርና ተቃውሞ የተሰማበት ነበር።ተማሪዎቹ “ቢመችሽም ባይመችሽም ሸገር ፊንፊኔ አትሆንልሽም፣ ያም ሄደ ይኸም መጣ ለውጥም አላመጣ፣ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም” የሚሉ መዝሙሮች ሲያሰሙ አርፍደዋል።

ይህም ብቻ አይደለም ደፋሩ የኦሕዴድ መራሹ መንግሥትና የከተማ አስተዳደር ታላላቅና መካከለኛ እንዲሁም አነስተኛ ሆቴሎች ባለቤቶች፣አነስተኛ የችርቻሮ ሱቆች ሳይቀሩ በተለይም በአማራ ተወላጆች ላይ ሊከፍሉ የማይችሉትን ግብርና ኪራይ በመጣሉ እዬነጠቀ ለሚፈልገው እንዲሸጡ አድርጓል። ሽያጩ ለኦሮሞዎች እንዲሆን ብድር የማግኘቱን ሂደት ያመቻቸ ለመሆኑ የወጡ ሚስጥሮች ያጋልጣሉ። በእጃዙር የኦሮሚያ መንግሥት ንብረት የማድረጉ አሻጥር የሌላው ጎሳ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ነው ሲሉ የመከራው ሰለባዎች ይናገራሉ።ገበያና ሰላም በጠፋበት፣ኑሮ በተወደደበት በዚህ ከባድ ወቅት የማይችሉትን ግብርና ኪራይ መጠዬቅ ባለይዞታዎቹን ለመንጠቅና ለማባረር እንደሆነ አያጠራጥርም። ሌላው የአዲስ አበባን የመሰልቀጥ እርምጃ የሚያሳዬው ሰሞኑን አቃቂ በተባለው ክፍለከተማ የሚኖሩትን ሰብስቦ ከአሁን በኋላ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች ናችሁ ማለቱ ነው።

የከተማዋን ነዋሪ ብቻም ሳይሆን የከተማዋን ገጽ ለማጥፋት የመሥራቾቿን ታሪክ የማጥፋቱም ዘመቻ የዚሁ የኦሮሙማው አገር ምስረታው አካል ነው። በሰሞኑ በሚኒሊክ ሆስፒታል አብይ አህመድ ይመጣል ተብሎ መግቢያው ላይ የነበረው የአጼ ሚኒልክ ስም ከተጻፈበት ድንጋይ ላይ እዬፈለፈሉ

ሲያወጡና ሲያሰግዱ ያዬንበት ሳምንት ነው።በሐረር ከተማ የራስ መኮንን ሃውልት ፈራርሶ ሙጃ እንደ በቀለበት፤የአራት ኪሎው የአጼ ምንሊክ ቤተመንግሥት ከበሩ ላይ አንበሳ ምስሉ ተነስቶ ፒኮክ እንደተቀመጠበትና ግቢው የመዝናኛ ቦታ እንደተሰራበት፣የታሪክ ቅርስ ቦታዎች እዬፈራረሱ የንግድ ሱቅ እንደሚሰራባቸው---ወዘተ ስናይ ነገ የአጼ ምንሊክ ሃውልት ላለመፍረሱ ዋስትና የለም።ቀስ በቀስ እያላመዱ አገር የመጠቅለሉን ጉዞ ተያይዘውታል።የሕዝቡን ትኩረት ለማስለወጥ የተለያዩ ጉዳዮችን እዬደነቀሩ መሄዱ የተለመደና ሕዝብ ያወቀው የጅል ፈሊጥ ሆኗል።ይህ ሁሉ መፈታተን ለውድቀት እንጂ ለመሰንበት አይረዳም።

ሌላው የታዘብነው ጉዳይ የቀድሞው የወያኔ መሪ የነበረው የሟቹ መለስ ዜናዊ ሚስት፣የኤፈርት የተባለው የዘረፋ ድርጅት አስተዳዳሪ የነበረችው አዜብ መስፍን በአራት ሽህ ብር ገቢ የምኖር ደሃ ነኝ ብላ ያሳቀችን ሳይረሳ፣ ለፈጸመችው የስርቆትና የፖለቲካ ወንጀል ሳትጠዬቅ  በአብይ አህመድ ውሳኔ በነጻ ወጥታ  አሜሪካ አገር ሰርቃ በገዛችው ትልቅ ቪላ እንድትኖር መደረጉ ሲገርመን ከቀናት በፊት ደግሞ በኡጋንዳ በሃይል ዘርፍ(Energy Sector) ብዙ ሚሊዮን ዶላር ለማፍሰስ መወሰኗ ተሰምቷል። ኢትዮጵያና ሕዝቧ በምን አይነት መሪዎች መዳፍ ስር ወድቀው እንደኖሩና እንዳሉ አመላካች ነው። ይህችው ሌባ ከአሜሪካ ባለስልጣኖች ጋር በነበራት የጥቅም ትስስር በነጻ እንድትወጣና በብዙ ሚሊዮን ዶላር በሚገመተው በገዛችው ቪላ ውስጥ እንድትኖር ያደረጓት እንደ ሱዛን ራይስ የመሰሉ ወዳጆቿ የተጫወቱት ሚና እንዳለ ብዙዎች በቦታው የሚኖሩና የሚከታተሉ ኢትዮጵያኖች የሚመሰክሩት ነው። ሌሎቹም በዚህ መልክ ዘርፈው በአሜሪካና አውሮፓ ቤትና ንብረት እንዲሁም የድርሻ ባለቤት(Share Holders) እንደሆኑ ያደባባይ ሚስጥር ነው።የሌባ ተቀባይ የሆነ ስለሌብነት ወንጀል መሆንና ስለፍትሕ መናገር አይችልም። የምዕራባውያን አገሮች ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ ያለው ሰው አገራቸው ገብቶ ብሎም ዜግነት ይዞ መኖር እንደሚችል መመሪያ አውጥተዋል።ያ ማለት የአፍሪካ፣የኤዥያና፣የሌሎቹም ደሃ አገር  ሌባ መሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ያገራቸውን ሃብት ዘርፈው ቢመጡ ማንም እንደማይነካቸው ነው።የካፒታሊዝም ዋናው መርህ ማጭበርበርና መዝረፍ በመሆኑ ሌቦችን አቅፎና ደግፎ መቆሙ ብዙም ሊደንቀን አይገባም።የካፒታሊዝም አንዱ መንገድ ወረራና ቅኝ ግዛት ለዘረፋና ለስርቆት መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል።አሁንም አገራትን በቀጥታና በእጅአዙር ለመውረርና ለመዝረፍ ዝግጅቱ ይበልጥ ተጠናክሯል።በተግባርም እዬታዬ ነው።ሌቦችን ማስጠጋት በአውሮፓውያን ብቻ ሳይሆን በአፍሪካና በሌሎቹም አገሮች የተለመደ ሆኗል።

መንግሥቱ ሃይለማርያም  የተባለው አምባገነን ሳይቀር የዚችን ድሃ አገር ካዝና አራቁቶ በደሃዋ ያፍሪካ አገር በዝምባቢዌ ታዋቂ ሚሊዬነር ለመሆን ችሏል።ጋዳፊ ለኢትዮጵያ የሰጠውን 150 ሚሊዮን ዶላር ዘርፎ  ለዚሁ ተግባር ዚምባብዌ አምባሳደር አድርጎ በላከው በአንቱ በአስራት ወልዴ በኩል ሰፊ መሬት፣ሕንጻዎችና የሚኖርበትን ባለ ሰፊ ግቢ ቪላ ቤት ገዝቷል።ሌባ ሲሰርቅ ይስማማል ሲካፈል ይጣላል እንደሚባለው ፣መንግሥቱ ሃይለማርያምም አባባሉን በቃላትና በተግባር ደግሞታል። ከአንቱ ከአስራት ወልዴ ጋር በዚሁ በተሰረቀ ብር ክፍፍል ምክንያት ድብልቅልቃቸው እንደወጣና እንደተለያዩ የሚያውቁ መስክረዋል።ሕግና መብት የሚያስከብር መንግሥት በኢትዮጵያ ስላልመጣ መንግሥቱም ሆነ ሌሎቹ ሌቦች ያሻቸውን አድርገው ሳይጠየቁ ኖረዋል፤እዬኖሩም ነው።የወደፊቱ ሕዝባዊ ሥርዓት ግን ሌቦችን ከያሉበት አድኖ ለፍርድ የሚያቀርብና ዳግም ሌቦች እንዳይኖሩ ያደርጋል።

ከላይ እንደገለጽነው በአገራችን የፖለቲካ  ሰማይ ላይ  የለውጥ ሞገድና ሙብረቃማ ደመና መኖሩን የሚያመላክቱ እንቅስቃሴዎች ያዬንበት ሳምንት ነው።ሕዝቡ፣ተነሳስቷል፤ጉምጉሙ በዝቷል።መምህሩ፣ ተማሪው፣ሃኪሙ፣ነጋዴው፣ቄሱ፣ሼሁ፣አርሶ አደሩ ፣ወታደሩ ሳይቀር በስርዓቱ ላይ ጥያቄ ከማንሳት ባለፈ እምቢ የማለት አቋም እያሳዬ ነው።

ለብዙ ጊዜ ድምጻቸውን አጥፍተው የነበሩ ወይም ስርዓቱን ደግፈው የቆሙ  የተቃዋሚ ፓርቲዎች የተቃውሞ መግለጫ ማውጣት ጀምረዋል።ምንም እንኳን ሥርዓቱ መለወጥ አለበት የሚል ጠንካራ ይዘት ያለው ባይሆንም መንግሥት “ሕግ የማስከበር  ዘመቻ”በሚል ሽፋን እያደረገ ያለውን ጭፍጨፋና ማሳደድ መቃወማቸው ከሌላው ጊዜ ለዩት ያደርጋቸዋል።ይህ ሌሎቹንም ሊቀሰቅስ ይችላል የሚል ግምት አለን።ተቃውሞው መንግሥት እርምጃውን አለሳልሶ ይግዛ የሚል ሳይሆን ሥልጣኑን ለሕዝብ ያስረክብ፣የኅሳ ፖለቲካ ይወገድ፣ክልላዊ አወቃቀር ይፍረስ የሚል ስር ነቀል ይዘት ያለው መሆን ይገባዋል። ያንንም በተግባር ለመግለጽ የሚያደርጉትን የመጠላለፍ ባህል ትተው፣የጋራ ግንባር በመፍጠር የሕዝቡን ትግል ሊቀላቀሉ ይገባል።ከሌሎቹ የፖለቲካ ድርጅቶችና የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ተባብረው የጋራ አመራርም መፍጠር ይኖርባቸዋል።

በሴቶችና በቀሳውስት በኩልም የምልጃ ጥሪ ለመንግሥትና ለወያኔ መቅረቡን ታዝበናል።ምንም እንኳን ሰላም አውርዱ የሚለውን ጥሪና ጥያቄ ባንቃወምም በሁለቱ አገር አጥፊዎች መካከል የሚደረግ እርቅ ዘላቂ ሰላም እንደማያመጣና እንደውም በባሰ ደረጃ ሃይላቸውን አስተባብረው ሥርዓቱን ለማቆዩት እንደሚረዳቸው መገንዘብ አስፈላጊ ነው።እነዚህ ሃይሎች እስካሉ ድረስ አገር እንዳገር ሕዝብም እንደ ሕዝብ በሰላምና በአንድነት አይኖሩም። ለዘለቄታ ላለው ሰላምና አንድነት እነዚህና መሰሎቻቸው የኅሳ ፖለቲካ አቀንቃኞችና አስተሳሰባቸው ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካ መሬት ተጠራርጎ መውጣት አለበት።የጥገና ለውጥና የወንበዴዎች መቀራረብና መስማማት ያገራችንን ችግር አያቃልልም፣ የሕዝቡንም ጥያቄ አይመልስም። በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን፣በኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ የሚኮራ፣የኢትዮጵያን ዳር ድንበር የሚያስከብር፣ለዴሞክራሲና ለፍትህ  መስፈን የሚተጋ፣የኅሳ ፖለቲካና አስተሳሰብን የሚጠዩፍ፣የክልል አወቃቀርን የሚያፈርስና ዴሞክራሲያዊ የክፍለሃገርን አወቃቀር የሚዘረጋ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ዘላቂ መፍትሔ ይሆናል።

አፈናና ማሳደዱ ይቁም! የታሠሩት ይፈቱ!!ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡ!!!

ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት!!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!!!